404

ብርሃንና ሰላም
BERHANENA SELAM
HAILE SELASSIE I PRINTING PRESS

# መዝሙር ሐዋዝ ፤

ሰብሕዎ
ለእግዚአብሔር
ስብሐተ ሐዲሰ ።
(መዝ. ፻፵፱ ቍ. ፩)

ሠናየ ዘምሩ
ወየብቡ ሎቱ ።
(መዝ. ፴፪ ቍ. ፫)

ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት ተዘጋጀ ።

አዲስ አበባ መስከረም ፳፫ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም.

www.ethiopianorthodox.org

# መዝሙር ፤

ኢኦተሐድ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት ።

አዲስ አበባ ፤

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፴፰ኛው ዘመነ መንግሥት ፡
ብርሃንና ሰላም ቀ. ኃ. ሥ. ማተሚያ ቤት
መስከረም ፳፫ ቀን ፲፱፻፷ ዓ. ም. ታተመ ።

www.ethiopianorthodox.org

## መ ቅ ድ ም ፤

እግዚአብሔር ጥንት የነበረ ፤ አሁንም ያለ ፤ ወደፊትም የሚኖር አምላክ ስለሆነ በጥንታዊውም በአዲሱም መዝሙር ይመሰገናል ። ራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ አዲስ መምህር ሁኖ በቀረበና አዲስ ሕግ በሠራ ጊዜ አዲስ መዝሙር ዘምሯል ፤ ( ማቴ- ፳፮ ) በየዘመኑ የተነሡ ነቢያት ቅዱሳን ፤ ሐዋርያት ፤ እንዲሁም ሊቃውንት ሁሉ እግዚአብሔርን በዚያው በነርሱ ዘመን በመሰላቸውና ደስ ባሰኛቸው በአዲስ መዝሙር ማመስገን እንደሚገባ ጽፈዋል ።

ለዚህም አስረጂ ነቢዩ ዳዊት « ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ » እግዚአብሔርን በአዲስ ምስጋና አመስግኑት ሲል አዟል ( መዝ ፻፵፱- ቁ- ፩ ) ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ልዑል እግዚአብሔርን በዚያኑ ጊዜ ሕዝብ ሁሉ በአዲስ ምስጋና ማመስገን እንደሚገባ « በምትሰበሰቡበት ጊዜ ለያንዳንዱ መዝሙር አለው » ሲል ጽፏል ። ፩ኛ/ ( ቆሮ- ፲፬-፳፮ ) በኋላ ዘመን የተነሡ ቅዱሳን አባቶችም የቅዳሴ ፤ የውዳሴ መጻሕፍት እንደጊዜው አበርክተዋል ፤ በዚያም ጊዜ ብቻ ሳይሆን አሁንም ቢሆን እኛ በልዩ አቅድ በአዲስ መዝሙር እግዚአብሔርን ማመስገን እንደሚገባን ይህ ሁሉ አስረጂ ይመራናል ። ይኸንንም በመከተል በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ሥር የሚካሔደው የኢትዮጵያ

www.ethiopianorthodox.org

ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅታችን ወጣቶችን በልዩ ልዩ ቦታ እየሰበሰበ ማስተማር ተግባሩ አድርጎ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ለወጣቶቹ ተስማሚ ፤ ጊዜውንም የመሰለ ፤ እንደዚህ ያለ አዲስ መዝሙር ማዘጋጀት ግድ ሆነበት ፤ ምክንያቱም ወጣቱ ደስ በሚለው ዜማና በሚገባውም ቋንቋ በሚያስደስተው የዘመረ እንደሆነ ልቡም መንፈሱም አብሮ ይዘምራል ። ለዚህም አስረጂ ቅዱስ ጳውሎስ ( በመንፈስ እዘምራለሁ ። በአእምሮም ደግሞ እዘምራለሁና ) ሲል ጽፏል ። ( ፩- ቆሮ- ፲፬-፲፭ ) ወጣቶችም በዚህ ካቴድራል አካባቢ የሚሰበሰቡት ብቻ ሳይሆኑ የድርጅቱ ቅርንጫፍ በተቋቋመበት በልዩ ልዩ ቦታዎች በአዲስ አበባና በአካባቢው ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ስለሚዘምር « በቃል ያለ ይረሳል ፤ በጽሑፍ ያለ ግን ይወሳል » በተባለው አባታዊ ምሳሌ መሠረት ይህን አዲስ መዝሙር አትመን ለወጣቱ እናበረክታለን ። ለመጀመሪያ ጊዜ መዝሙር እንድናዘጋጅ ምክንያት የሆነ የማኅበረ ክርስቶስ ( የቤት ልጅ ዕድገት ) ማኅበርን እና መሰግናለን ። እንዲሁም በግል ችሎታቸው ድርሰቱን ከዜማው ጋር አቀናብረው ለሰጡን ለድርጅቱ መምህራን ከፍ ያለ ምስጋናችን እናቀርባለን ።

ወጣቶችም በዚሁ መሠረት በእሑድ ትምህርት ቤት በተሰበሰባችሁ ጊዜ አምላካችሁን በዚህና ይህን በመሳሰለው ሁሉ እንድታመሰግኑት እናሳስባለን ።

## ማ ው ጫ ፤


| አርእስት | የክፍል ብዛት | ገጽ |
|---|---|---|
| የዘመን መለወጫ መዝሙር | ፪ | ፯ |
| የመስቀል - - - - - | ፩ - - - - - | ፲፩ |
| የወርኃ ጽጌ - - - - | ፬ - - - - - | ፲፪ |
| የዘመነ ስብከት - - - | ፩ - - - - - | ፲፮ |
| የልደት - - - - - - | ፫ - - - - - | ፲፰ |
| የጥምቀት - - - - - | ፰ - - - - - | ፳፩ |
| የቃና ዘገሊላ - - - - | ፩ - - - - - | ፳፯ |
| የጾም - - - - - - | ፪ - - - - - | ፳፰ |
| የሆሣዕና - - - - - | ፮ - - - - - | ፴ |
| የስቅለት - - - - - | ፪ - - - - - | ፴፫ |
| የትንሣኤ - - - - - | ፲፫ - - - - - | ፴፰ |
| የጰራቅሊጦስ - - - - | ፫ - - - - - | ፵፫ |
| የሰንበት - - - - - - | ፪ - - - - - | ፵፬ |
| የጸሎት - - - - - - | ፩ - - - - - | ፵፯ |




www.ethiopianorthodox.org

| አርእስት | የክፍል ብዛት | ገጽ |
| --- | --- | --- |
| የክረምት | ፱ | ፵፰ |
| መዝሙረ ንስሐ | ፫ | ፵፱ |
| የእመቤታችን | ፮ | ፶፩ |
| የደብረ ታቦር | ፩ | ፶፮ |
| የቤተ ክርስቲያን | ፫ | ፶፮ |
| የዘወትር | ፲፫ | ፶፰ |
| የቅዱሳን | ፩ | ፷፩ |
| የአብርሃም | ፩ | ፷፱ |
| የምጽአት | ፩ | ፷፫ |




www.ethiopianorthodox.org

# የ ዘ መ ን መ ለ ወ ጫ
# መ ዝ ሙ ር

## ክፍል ፩ ፤

የዕለት የዓመት የዘመናት ጌታ
ከዚህ ካደረስከኝ ዘመኔን ሳትገታ
አቀርብልሀአለሁ የክብር ሰላምታ ።

ኑ እናመስግን ከልባችን የሰማዩን አባታችን
ከዚህ ዕለት ከዚህ ዓመት ካደረሰን ሁላችንን ።

የሰው ልጆች ዕድሜ ጥንቱንም ሲጀመር
ምን ቢወጣ ቢወርድ ቢበዛ ቢደመር
አንድ ቀን አይሞላም እንዳንተ አቈጣጠር ።

ኑ እናመስግን ከልባችን የሰማዩን አባታችን
ከዚህ ዕለት ከዚህ ዓመት ካደረሰን ሁላችንን ።

ስለዚህ አምላክ ሆይ ክቡር ነው ቅዱስ ነው
ወዳንተ እንዲመለስ ቀን የሰጠኸው ሰው
ደካማ ነውና ሰው ዕድሜ ከራበው ።

ኑ እናመስግን ከልባችን የሰማዩን አባታችን
ከዚህ ዕለት ከዚህ ዓመት ካደረሰን ሁላችንን ።

በከንቱ ጊዜያችን ፈጽሞ እንዳይጠፋ
በርትተን ከሠራን ያለአንዳች ነቀፋ
አምላክ የሚሰጠን አለን ፍጹም ተስፋ ።

ኑ እናመስግን ከልባችን የሰማዩን አባታችን
ከዚህ ዕለት ከዚህ ዓመት ካደረሰን ሁላችንን ።

ከንቱ ካሳለፍኩት ጊዜዬን በዋዛ
ምን ያደርግልኛል ዘመኔ ቢበዛ
ደግሞም በጠቅላላው ዓለምን ብገዛ

ኑ እናመስግን ከልባችን የሰማዩን አባታችን
ከዚህ ዕለት ከዚህ ዓመት ካደረሰን ሁላችንን ።

ወርኃ ክረምት አልፎ መስከረም ሲጠባ
ምድር በልምላሜ ስታጌጥ በአበባ
እናምናለን ላንተ ምስጋና እንዲገባ ።

ኑ እናመስግን ከልባችን የሰማዩን አባታችን
ከዚህ ዕለት ከዚህ ዓመት ካደረሰን ሁላችንን ።

ከተሾመ ዘርይሁን



## ክፍል ፪ ፤

እናስታውስ ምእመናን እናስታውስ
መታደስ አለበት ክርስቲያን በመንፈስ ፤
ያምላካችን ትእዛዝ አንዱንም ሳንፈጽም
ክርስቲያን መባሉ ምንም አይረዳንም ፤

እናስታውስ ምእመናን እናስታውስ
መታደስ አለበት ክርስቲያን በመንፈስ ።
የመረረው ጣፋጭ ጣፋጩም መራራ
ዛፍ ለምንም ዓይነት ከቶ እንዳያፈራ ፤
እንኳንስ ተነግሮ በአምላካዊ ቃል
ሁሉም በማስተዋል ሊረዳው ይችላል ።

እናስታውስ ምእመናን እናስታውስ
መታደስ አለበት ክርስቲያን በመንፈስ ።
ይህ ታላቅ ምሳሌም የተሰነዘረው
ለታላቁ ፍጡር በተለይ ለሰው ነው ፤
የሚያጠግብ ፍሬን ለመስጠት የቻሉ
ብናስታውሳቸው ብዙ ሰዎች አሉ ።

እናስታውስ ምእመናን እናስታውስ
መታደስ አለበት ክርስቲያን በመንፈስ ።
ዮሐንስ ለዚህ ክብር ሊበቃ የቻለው
በታወቁት ተክሎች በወላጆቹ ነው ፤



www.ethiopianorthodox.org

እናስታውስ ምእመናን [እናስታውስ
መታደስ አለበት ክርስቲያን በመንፈስ ።

የመንፈስ ጠል ያለው ዮሐንስ አትክልትም
ፍሬው አጥጋቢ ነው እስከ ዘለዓለም ፤
ዮሐንስ ለክብሩ ምንም ወሰን የለው
ነቢዩ ሰማዕቱም ጻድቁም እሱ ነው ።

እናስታውስ ምእመናን እናስታውስ
መታደስ አለበት ክርስቲያን በመንፈስ ።

የመንፈስ እድገትም ለሰው የሚሰጠው
እምነትና ሥራ ካንድ ላይ ሲገኝ ነው ፤
ይህንንም ምኞት እንዲፈጽምልን
አምላክን በጸሎት መለመን አለብን ።

እናስታውስ ምእመናን እናስታውስ
መታደስ አለበት ክርስቲያን በመንፈስ ።

ሁሉን የምትችል ይቅር ባይ አምላክ ሆይ
በተሰጠን ዕውቀት ተባብረን ስንጸልይ ፤
ምንም እኛ ሰዎች ኃጢአት ባይለየን
ይቅር ባይ ነህና አንተ ይቅር በለን ።

እናስታውስ ምእመናን እናስታውስ
መታደስ አለበት ክርስቲያን በመንፈስ ።

ከአእምሮ ማንደፍሮ



## የመስቀል መዝሙር ፤

እርስ በርሳችን እንዋደድ
ይህ ነውና ጥሩ መንገድ
መስቀሉን ተሸክመን በእምነት እንራመድ
ሽልማትን እንድንወስድ እንጓዝ ወደርሱ ዘንድ ።

በዓይኑ የሚያየውን
የማይወድ ባልንጀራውን
እወዳለሁ ቢል ፈጣሪውን
አይቶ የማያውቀውን ፤

ነው እንጂ ሐሰተኛ
አይደለም እውነተኛ ፤

ፍቅር ቢኖር በኛ መሐል
ጥል ከሥሩ ይነቀላል
ኑሯችንም ይሻሻላል
ሸክማችንም ይቃለላል ፤

ምንጊዜም ስላለን ተስፋ
ሥራችንን እናስፋፋ ፤

እንዳይለየን ያምላክ ምሕረት
ፅናት ያሻል በሃይማኖት
እንድናገኝ ፍቱን መድኃኒት
እናቅርብ ለሱ ስብሐት ፤



www.ethiopianorthodox.org

ተባብረን እንድንሠራ
አምላክ ይሁን ከኛ ጋራ ።

ከነቢያ ልዑል ዮሐንስ

## የወርኃ ጽጌ መዝሙር ፤

### ክፍል ፩ ፤

ይመስገን አምላክ ይመስገን ( ፫ ጊዜ )
በውነት ካስተዋልን በብሩህ ልቡና
እንደምን ያንሰዋል ለአምላክ ምስጋና ፤
የሚያመሰግነው ብልህ ሰው አምላኩን
እያስተዋለ ነው ሥነ ፍጥረቶችን ።
ይመስገን አምላክ ይመስገን ( ፫ ጊዜ )
ውኃ ቦታ ሲለቅ ምድር ስትታደስ
አሮጌውን ትታ አዲሱን ስትለብስ ፤
ክረምት ሲወጣ መስከረም ብቅ ሲል
በጕልሕ ይታያል የአምላካችን ኃይል ።
ይመስገን አምላክ ይመስገን ( ፫ ጊዜ )
ሳይወጡ ሳይወርዱ ሳይፈትሉ ሳይሠሩ
ዕፀዋት አጊጠው ለብሰው የሚኖሩ ፤
ክርስቶስ በወንጌል እንደተናገረው
በቸርነቱ እንጂ ከምን አምጥተው ነው ።



ይመስገን አምላክ ይመስገን ( ፫ ጊዜ )
በሥነ ተፈጥሮ ባገኘው ዕውቀቱ
በበጋ ሰብስቦ ምግቡን ለክረምቱ ፤
በአንዲት ዋሻ ሆኖ ያሳለፈው ሁሉ
ይህ ወራት ሲሸተው ይወጣል በሙሉ ።
ይመስገን አምላክ ይመስገን ( ፫ ጊዜ )
አምላክ ይህን ሁሉ በሕግ ያዘጋጃል
አራዊት እንስሳት ያመሰግኑታል ፤
ሰውሳ ብልሁ በጉልሕ ዕውቀቱ
ያመሰግናል ወይ ጌታውን በውነቱ ።
ይመስገን አምላክ ይመስገን ( ፫ ጊዜ )
ሰማይን በኮከብ ምድርን በአበባ
ለሚሸልም አምላክ መስከረም ሲጠባ ፤
ምድርም ፍሬ እንድትሰጥ ለሚባርክ ጌታ
ምስጋና ይገባል በጧት በማታ ።
ይመስገን አምላክ ይመስገን ( ፫ ጊዜ )

ከአእምሮ ማንደፍሮ

### ክፍል ፪ ፤

ትዌድሶ መርዓት ወትብሎ ( ፪ ጊዜ )
ወልድ እኁየ ቃልከ አዳም ( ፪ ጊዜ )



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፫ ፤

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ( ፬ ጊዜ )
ሖረገ ወይን
እንተ በምድር ሥረዊሃ
ወበሰማይ አዕፁቂሃ
ሖረገ ወይን
እንተ በሥሉስ ትትገመድ ወታፈሪ ለነ አስካለ በረከት
ሖረገ ወይን
ሲሳዮሙ ለቅዱሳን
ሖረገ ወይን
ሠርዐ ሰንበተ በቃሉ ወፀገወ ሰላመ ለኩሉ ።

## ክፍል ፬ ፤

ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ
ናሁ አስተርአየ ጽጌ መርዓቱኒ ትቤ
ወልድ እኁየ ይምዕዝ ከርቤ
ናሁ አስተርአየ ጽጌ
ዕንባቆም ነቢይ ግብረ ምግባሩ ለወልድ አንከርኩ ይቤ
ናሁ አስተርአየ ጽጌ
ንጉሠ ሰላም ክርስቶስ ዐቢይ ልዕልናከ
ወመንክር ስብሐቲከ ለዕረፍት ሰንበተ ሠራዕከ ።
( መዝሙረ ያሬድ )



## የዘመነ ስብከት መዝሙር ፤

የነቢያት ዜና በእምነት ጎዳና ( ፪ ጊዜ )
የእግዚአብሔርን ሰዎች እስኪ እናስታውሳቸው
ይኸው ለዘለዓለም ያበራል ሥራቸው ።
የነቢያት ዜና በእምነት ጎዳና ( ፪ ጊዜ )
ዓለም ስታሰጥም ብዙውን ተላላ
ምንም ሳይመኙ ኃላፊውን ተድላ ።
የነቢያት ዜና በእምነት ጎዳና ( ፪ ጊዜ )
በምኞት ሳይረክሱ አገኝ አጣ ብለው
ምርጥ ዕቃዎች ሆነው በመገኘታቸው
የነቢያት ዜና በእምነት ጎዳና ( ፪ ጊዜ )
የእግዚአብሔር መንፈስ በነርሱ ላይ አድሮ
ለኋለኛው ትውልድ ተናግሯል ዘርዝሮ ።
የነቢያት ዜና በእምነት ጎዳና ( ፪ ጊዜ )
የእውነት ምስክሮች ብፁዓን ነቢያት
ይወለዳል ብለው አምላክ ለሰው ድኅነት ።
የነቢያት ዜና በእምነት ጎዳና ( ፪ ጊዜ )
ዙረው ሲያስተምሩ ሲያስረዱ ዘርዝረው
በመንፈስ ከኛ ጋር አብረው ተባብረው ነው ።



www.ethiopianorthodox.org

የነቢያት ዜና በእምነት ጐዳና ( ፫ ጊዜ )

ይኸው ከደኅና ምንጭ የተገኘው ዜና
ዓለሙን ሊዋጀው ድኆችን ሊያጽናና ።

የነቢያት ዜና በእምነት ጐዳና ( ፪ ጊዜ )

በአትሕቶ ሲወርድ በመጠን ሲወሰን
ለተቀባይ ደስታ ለዕንቢተኛው ኀዘን ።

የነቢያት ዜና በእምነት ጐዳና ( ፪ ጊዜ )

በነቢያት ዜና ቀድሞ እንደታመነ
ይኸው በጠቅላላው ያለም ብርሃን ሆነ ።

የነቢያት ዜና በእምነት ጐዳና ( ፪ ጊዜ )

ልጅህን እንደላክ አምላክ ለዓለም ድኅነት
አሁንም ለሰው ልጅ በደሉን ተውለት ።

የነቢያት ዜና በእምነት ጐዳና ( ፪ ጊዜ )

ከአእምሮ ማንደፍሮ

## የልደት መዝሙር ፤

### ክፍል ፩ ፤

በጎል ሰከበ በአጽርቅት ተጠብለለ
ውስተ ማኅፀነ ድንግል ኀደረ
ዮም ተወልደ እግዚእ ወመድኅን ቤዛ ኵሉ ዓለም ፤



### ክፍል ፪ ፤

እፎ ተገምረ ውስተ ማኅፀነ ድንግል ( ፪ ጊዜ )
ዘሰማየ ሰማያት ኢያገምሮ ኢያገምሮ ዘሰማየ ሰማያት ።
( ፪ ጊዜ )

( መዝሙረ ያሬድ )

### ክፍል ፫ ፤

የዓለም መድኀኒት የተወለደብሽ
አንቺ ቤተ ልሔም የተቀደስሽ ነሽ
የአማልክት አምላክ ንጉሠ ነገሥት
ኃያላን በሙሉ የሚሰግዱለት
በጨርቅ ተጠቅልሎ ተኛ ከበረት ።

የዓለም መድኃኒት የተወለደብሽ
አንቺ ቤተ ልሔም የተቀደስሽ ነሽ
ዓዋቂዎች ሁሉ በቅን አሳባቸው
ወደ አንቺ ተጓዙ ኮከብ ሲመራቸው ።

የዓለም መድኀኒት የተወለደብሽ
አንቺ ቤተ ልሔም የተቀደስሽ ነሽ ።
ለተከታይ ትውልድ ምሳሌ በመሆን
ሰግደው ገበሩለት ወርቅ ፤ ዕጣን ፤ ከርቤን ፤

የዓለም መድኀኒት የተወለደብሽ
አንቺ ቤተ ልሔም የተቀደስሽ ነሽ ፤



www.ethiopianorthodox.org

የሚያድለው ጌታ ዕውቀት ለሕፃናት
የሚመሰገነው በአራ መላእክት
ከእንስሳት ጋራ አደረ ከበረት ፤

የዓለም መድኀኒት የተወለደብሽ
አንቺ ቤተ ልሔም የተቀደስሽ ነሽ

በሥጋ ተገልጦ ረቂቅ ምሥጢሩ
ሰውና መላእክት ካንድ ላይ ዘመሩ ።

የዓለም መድኀኒት የተወለደብሽ
አንቺ ቤተ ልሔም የተቀደስሽ ነሽ ፤

ከአእምሮ ማንደፍሮ

## ክፍል ፬ ፡

ንጉሥ ተወለደ የዓለም መድኃኒት
መርገምን መለሳት ወደሥርየት
ሔዋንን አወጣት ከሲኦል እስራት
ባለ ግምጃ ጥላ ሆነች እመቤት ፤
እርሱ ባይወለድ ቸር አባታችን
እርሱ ባይወለድ መድኃኒታችን
አትገኝም ነበር ገነት ምድራችን ፤
ሰላም፣ለናንት ይሁን በዚህ ላላችሁ
የክርስቶስን ቃል እንደሰማችሁ ፤



የሕይወት ደስታ የተስፋ መሠረት
አንድነት ይስጣችሁ የሰው ልጅ አባት

እርሱ ባይወለድ ቸር አባታችን
እርሱ ባይወለድ መድኃኒታችን
አትገኝም ነበር ገነት ምድራችን ።

ገና በልጅነት ሃይማኖት ሲጀመር
አስደሳች ይሆናል ለኋለኛው ተግባር
በርቱና እናጥና ሃይማኖታችንን
ክርስቶስ ሰጥቶናል ዓለም አዲስን ።

እርሱ ባይወለድ ቸር አባታችን
እርሱ ባይወለድ መድኃኒታችን
አትገኝም ነበር ገነት ምድራችን ።

በልጅነት ሰዓት ብዙ የደከመ
ዋጋውም ከፍ አለ ዕድሜው ረዘመ ።
አይዟችሁ ወጣቶች እንሥራ በዕድሜያችን
ክርስቶስም ሙቷል ለኃጢአታችን ።

እርሱ ባይወለድ ቸር አባታችን
እርሱ ባይወለድ መድኃኒታችን
አትገኝም ነበር ገነት ምድራችን ።



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፫ ፤

በበረት ተኛ በጨርቅ ተጠቀለለ (፪ ጊዜ)
የዓለም መድኃኒት (፪) ዛሬ ተወለደ ። (፪ ጊዜ)

## ክፍል ፬ ፤

እስመ እምዘርዐ ዳዊት ዘመጽአ ( ፪ ጊዜ )
በቤተ ልሔም ዘይሁዳ ። ( ፪ ጊዜ )

## ክፍል ፭ ፤

ዮም ተወልደ መድኃኔ ዓለም (፪ ጊዜ )
ዮም ተወልደ ከሣቴ ብርሃን ። (፪ ጊዜ)
( መዝሙረ ያሬድ

## ክፍል ፮ ፤

ክብርና ሰላምን አንድነት አገኘን
መድኃኒታችን ተወልዷልና
ክብርና ሰላምን አንድነት አገኘን
በጨለማ ላሉት ብርሃን ወጣላቸው
መድኃኒታችን ተወልዷልና ።



## የጥምቀት መዝሙር ፤

## ክፍል ፩ ፤

ከላይኛው አገር ከሰማያት ወርዶ
ከድንግል ማርያም ዳግመኛ ተወልዶ
ድንግል ማርያም ሆይ ያስገኘሽው ፍሬ
ሕዝቦቹን ለማዳን ተጠመቀ ዛሬ
መለኮት ኃያሉ ተኝቶ በበረት
እጅ መንሻ አመጡለት ሦስቱ [ነገሥታት
ድንግል ማርያም ሆይ ያስገኘሽው ፍሬ
ሕዝቦቹን ለማዳን ተጠመቀ ዛሬ
ወደ አገራቸውም ሊመሔድ ሲነሡ
በሄሮድስ በኩል እንዳይመለሱ ፤
መላኩ ነግሯቸው እነሱም አምነው
በሌላ ጎዳና ገቡ አገራቸው ፤
ሰማይና ምድርን እንዳልደነገገ
ከሕፃናት ጋራ በገሊላ አደገ ።
ድንግል ማርያም ሆይ ያስገኘሽው ፍሬ
ሕዝቦቹን ለማዳን ተጠመቀ ዛሬ ።
ከግብፅም ሲመጣ ኖሮ በስደት
ናዝራዊ ለመባል ገባ ከናዝሬት



www.ethiopianorthodox.org

ድንግል ማርያም ሆይ ያስገኘሽው ፍሬ
ሕዝቦቹን ለማዳን ተጠመቀ ዛሬ
ሎሌ ወደ ጌታው ነው እንጅ የሚሔድ
ጌታ እንዴት ይመጣል ወደአገልጋዩ ዘንድ ፤
አጠምቅ ነበረ ባንተ ስም ሕዝብን
እንዴት ብዬ ላጥምቅ አንተን ጌታዬን ።
ድንግል ማርያም ሆይ ያስገኘሽው ፍሬ
ሕዝቦቹን ለማዳን ተጠመቀ ዛሬ
ከማቴ ብርሃን ወልዱ ለቡሩክ
ብለህ በመናገር አጥምቀኝ እያልክ ፤
ድንግል ማርያም ሆይ ያስገኘሽው ፍሬ
ሕዝቦቹን ለማዳን ተጠመቀ ዛሬ
እንደዚህ እያለ ሲያጠምቀው ከልብ
መንፈስ ቅዱስ መጣ በአምሳለ ርግብ ፤
ድንግል ማርያም ሆይ ያስገኘሽው ፍሬ
ሕዝቦቹን ለማዳን ተጠመቀ ዛሬ
ሉብም መሰከረ በደመና ሳለ
የምወደው ልጄ ይኸ ነው እያለ ፤
ድንግል ማርያም ሆይ ያስገኘሽው ፍሬ
ሕዝቦቹን ለማዳን ተጠመቀ ዛሬ ።

ከነቅዓ ጥበብ ወንድም



## ክፍል ፪ ፤

ፈለገ ዮርዳኖስ የእምነታችን ጣዕሙ
ለክርስቲያን ታሪክ አንቺ ነሽ መቅድሙ ።
አዲሱ ሙሽራ ሲመጣ እያያችሁ
የዮርዳኖስ ምንጮች ስለምን ሸሻችሁ
ፈለገ ዮርዳኖስ የእምነታችን ጣዕሙ
ለክርስቲያን ታሪክ አንቺ ነሽ መቅድሙ ።
እናንተስ ተራሮች እግር ሳይኖራችሁ
እንዴት እንደ ጊደር ሽቅብ ዘለላችሁ ።
ፈለገ ዮርዳኖስ የእምነታችን ጣዕሙ
ለክርስቲያን ታሪክ አንቺ ነሽ መቅድሙ
የግመል ደበሎ ለብሶ ስላያችሁ
መጥምቁ ዮሐንስ አውሬ መሰላችሁ ፤
ፈለገ ዮርዳኖስ የእምነታችን ጣዕሙ
ለክርስቲያን ታሪክ አንቺ ነሽ መቅድሙ
የአንበሳ ድምፅ ነው ወይንስ ደስታ
መቸ ተማራችሁ እንዲህ ያል ግርግርታ
ፈለገ ዮርዳኖስ የእምነታችን ጣዕሙ
ለክርስቲያን ታሪክ አንቺ ነሽ መቅድሙ



www.ethiopianorthodox.org

ቅድስት ዮርዳኖስ ሆይ የጌታ ሀገሩ
አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ባንቺ ላይ አደሩ ።
    ፈለገ ዮርዳኖስ የእምነታችን ጣዕሙ
    ለክርስቲያን ታሪክ አንቺ ነሽ መቅድሙ
ያለ ተፈጥሯቸው ወንዞች ዕልል ካሉ
ሊዘምር ይገባል የሰው ልጅ በሙሉ ።
    ፈለገ ዮርዳኖስ የእምነታችን ጣዕሙ
    ለክርስቲያን ታሪክ አንቺነሽ መቅድሙ ፤
ሰማያዊው አባት ፍቅሩን ስላሳየን
ጌታ በዮርዳኖስ ላንተ እንዘምራለን ።
    ፈለገ ዮርዳኖስ የእምነታችን ጣዕሙ
    ለክርስቲያን ታሪክ አንቺ ነሽ መቅድሙ
ጌታ ሆይ ያላንተ የለምና ሕይወት
ተጠምቀን ስንለምን ስጠን ዳግም ልደት ።
    ፈለገ ዮርዳኖስ የእምነታችን ጣዕሙ
    ለክርስቲያን ታሪክ አንቺ ነሽ መቅድሙ

ከአእምሮ ማንደፍሮ

## ክፍል ፫ ፤

የዓለምን በደል የሰውን ግፍ አይቶ
ዘጠና ዘጠኙን መላእክትን ትቶ
ጽድቅን ለመፈጸም በደልን አጥፍቶ



    የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
    አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለኛ ።
የሰማዮች ሰማይ የማይችለው ንጉሥ
ተወልዶ ሲጠመቅ እኛን ለመቀደስ
ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ እንደፈረስ ።
    የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
    አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለኛ ።
ባሕር ተጨነቀች ጠበባት መሬቱ
ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ
እንደ ተናገረው ዳዊት በትንቢቱ ።
    የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
    አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለኛ ።
ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሠርት
መጣ በደመና ሰማያዊው አባት
እየመሰከረ የልጁን ጌትነት ።
    የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
    አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለኛ ።
እንደምናነበው በወንጌል ተጽፎ
መንፈስ ቅዱስ ታዬ በራሱ ላይ አርፎ
በርግብ ምሳሌ ክንፉን አሰይፎ ።
    የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
    አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለኛ



www.ethiopianorthodox.org

ባሕር ስትጨነቅ ተራራው ሲጨፍር
ሰማዩ ሲከፈት ደመናው ሲናገር
ዓለም በዛሬው ቀን አየች ይህን ምሥጢር ።

የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ
አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለኛ ።

ከተሾመ ዘርይሁን

## ክፍል ፬ ፤

ሐዲጎ ተስዓ ወተሳተ ነገደ ( ፪ ጊዜ )
ቆመ ማዕከለ ባሕር ጉብዐ ወወጽአ በሰላም ( ፪ ጊዜ )

## ክፍል ፭ ፤

ነአምን በአብ ወነአምን በወልድ ( ፪ ጊዜ )
ወነአምን ( ፪ ጊዜ ) በመንፈስ ቅዱስ ( ፪ ጊዜ )

## ክፍል ፮ ፤

ሖረ ኢየሱስ እምገሊላ ኀበ ዮሐንስ ( ፪ ጊዜ )
ፈለገ ዮርዳኖስ ከመያጥምቆ ( ፪ ጊዜ )
( መዝሙረ ያሬድ )



# ለቃና ዘገሊላ የሚዘመር ፤

## ክፍል ፩ ፤

አዳምን ያልተወው እንደተሰደደ
እሰይ የምሥራች ዛሬ ተወለደ ፤
አምላካችን መድኃኒታችን
ተወለደ ለነፃነታችን
አዳምን ያልተወው እንደ ተጨነቀ
እሰይ የምሥራች ዛሬ ተጠመቀ ፤
አምላካችን መድኃኒታችን
ተወለደ ለነፃነታችን ፤
አዳምን ሊጠራ የመጣው ሙሽራ
በገሊላ መንደር ለሠርግ ተጠራ ፤
አምላካችን መድኃኒታችን
ተወለደ ለነፃነታችን ፤
ሠርግ ቤት እንዳለ በክብር ተቀምጦ
የወይን ጠጅ ሆነ ወኃው ተለውጦ ፤
አምላካችን መድኃኒታችን
ተወለደ ለነፃነታችን ፤
በገሊላ መንደር ይህን ታምር ሠራ
እጅግ ያስደንቃል የጌታችን ሥራ ፤



www.ethiopianorthodox.org

አምላካችን መድኃኒታችን
ተወለደ ለነፃነታችን ፤

ጌታችን አንድ ቀን ያደረገው ታምር
ሲያስደንቅ ይኖራል ይህን ሁሉ ፍጡር ፤

አምላካችን መድኃኒታችን
ተወለደ ለነፃነታችን ፤

## የጾም መዝሙር ፤

### ክፍል ፩ ፤

ተቀኑዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት
ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና
ጾምን እንጹም ሰውንም እናፍቅር

ተቀኑዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት ም. ለ.
ሰንበትን እናክብር ጽድቅንም እንፈጽም

ተቀኑዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት ም. ለ.
ከእህል ብቻ አይደለም ጾም መጾም
ክፉ ከመናገርም ነው እንጂ ።

ተቀኑዩ ለእግዚአብሔር - -
ፈተናውስ ለርሱም ለጌታችን አልቀረም

ተቀኑዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃትም ለዘለዓም ነውና ፤
ምሳሌውን ከርሱ ከጌታችን እንውሰድ

ተቀኑዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት ም. ለ.

ከአእምሮ ማንደፍሮ



### ክፍል ፪ ፤

ገዳመ ቆሮንቶስ የትምህርት ገበታ
በአንቺ ተፈተነ መምህርና ጌታ ።

አርባ መዓልትና አርባ ሌሊት ጹመህ
ሦስት ጥያቄዎች ፈታኝ ቢያቀርብብህ
በፍጹም ትሕትና ታግሠህ ለግሠህ
ለኛ አርአያ ልትሆን ፈተናውን አለፍህ

ገዳመ ቆሮንቶስ የትምህርት ገበታ
በአንቺ ተፈተነ መምህርና ጌታ ።

ጌታ ሆይ ፈታኝህ አንተ ያሳፈርኸው
ይፈታተነናል ዛሬም ከኛ ጋር ነው
በረቂቅ ጥበብህ በማንመረምረው
ድል አድራጊው ጌታ እባክህ ድል ንሣው ፤

ገዳመ ቆሮንቶስ - -
በአንቺ ተፈተነ - -

ይኸ ክፉ መንፈስ የማይታይ ጉልቶ
ትዕቢትና ስስት አሲድ ሁኖ ገብቶ
ሊፈጀን ነውና እርስ በርስ አጣልቶ
ጌታ ሆይ አሳየን ዝክረ ስሙ ጠፍቶ



www.ethiopianorthodox.org

ገዳመ ቆሮንቶስ - -
በአንቺ ተፈተነ - -
ሰው በእንጀራ ብቻ ሊኖር እንደማይችል
ለመጣብህ ፈታኝ በግልጽ አውጀሃል
ኃይል ስለሌለን በምንበላው እህል
አቤቱ አይለየን ዘወትር ያንተ ቃል
ገዳመ ቆሮንቶስ - -
በአንቺ ተፈተነ - -

## የሆሣዕና መዝሙር ፤

### ክፍል ፩ ፤

ሆሣዕና ዕምርት እንተ አቡነ ዳዊት ( ፪ ጊዜ )
ቡርክት እንተ ትመጽእ መንግሥት ( ፪ ጊዜ )

### ክፍል ፪ ፤

ይባዕ ንጉሠ ስብሐት ( ፪ ጊዜ )
ይባዕ አምላክ ምሕረት ( ፪ ጊዜ )
( መዝሙረ ያሬድ )

### ክፍል ፫ ፤

የዓለም መድኃኒት አጽዋምን ወስኖ
ያለም ንጉሥ ሲሆን እንደ ድኃ ሆኖ
ገባ ኢየሩሳሌም ባህያ ተጭኖ ፤



ሕዝቡም ተቀበሉት ሁላቸው በሙሉ
ዘንባባውን ይዘው ሆሣዕና እያሉ ፤
ለእሥራኤል ንጉሥ ለዓለም መድኃኒት
ሆሣዕና ብለው ደንጎች ዘመሩለት ።
ይህ ለሰዎች እንጂ ለደንጎች መች ነበር
ከነሱ እንዳንብስ በውነት እንጣጣር
አስተባብረን ይዘን ትሕትናን ከፍቅር ።
ከነቅዓ ጥበብ ወንድም

### ክፍል ፬ ፤

ሆሣዕና ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና በአርያም
ቅድስት ሀገር ሆይ ኢየሩሳሌም
ምስጋናሽ ብዙ ነው በመላው ዓለም ።
በአህያ ላይ ሆኖ ወዳንቺ የገባው
ኢየሱስ ክርስቶስ የዓለም መድኃኒት ነው ።
ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና በአርያም
ኃይልና ሥልጣንም ባንድ ላይ ስላለው
ጠላቶችሽ ፈሩ ሕዝብሽም ደስ አለው ።
ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና በአርያም



www.ethiopianorthodox.org

እናውቃለን ባዮች ግብዞች ሲቀሩ
ወጣት ሽማግሌ ሕፃናትም ሆነው ባንድነት ዘመሩ ።

ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና በአርያም
ሰውማ ቢዘምር ምን ያስገርመናል
ሆሣዕና ሰው ቀርቶ ድንጋይ ያናግራል ።

ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና በአርያም
ቅድስት ሀገር ሆይ ኢየሩሳሌም
ምስጋናሽ ብዙ ነው በመላው ዓለም

ከአእምሮ ማንደፍሮ

## ክፍል ፫ ፤

ወይቤላ ሶበ ተአምሪ ጽዮን
ነዋ ንጉሥኪ በጽሐ ብርሃንኪ
የም ሰላምኪ
ተፈሥሒ በሕዝብኪ
የም ሰላምኪ
ይትኃፈሩ ጸላእትኪ
የም ሰላምኪ
ሰላምኪ ሰላምኪ
የም ሰላምኪ ።

( መዝሙረ ያሬድ )



## የስቅለት መዝሙር ፤

## ክፍል ፩ ፤

ክርስቶስ ያንተ ሞት ለኛ ሕይወት ባይሆን
የሥቃይህ ነገር እንደምን በቆጨን ።
ራስ መውደድ ካለ ዓዋቂ ነኝ ማለት
አንድ ሰው አይችልም ለመኖር በሕይወት
ብናስታውሳቸው ያይሁድን ካህናት
ባለማወቅ ሳይሆን የኦሪትን ትምህርት
በምቀኝነት ነው ጌታን የሰቀሉት ፤

ክርስቶስ ያንተ ሞት ለኛ ሕይወት ባይሆን
የሥቃይህ ነገር እንደምን በቆጨን ።
በሰው እጅ መውደቅ ምንኛ ጭንቅ ነው
ባለመብት ሆኖ እርሙን ቢለምነው
የዝናሙን ጌታ ውሀ ከለከለው
ሐሞትና ከርቤ መጣጣም አጠጣው ።

ክርስቶስ ያንተ ሞት ለኛ ሕይወት ባይሆን
የሥቃይህ ነገር እንደምን በቆጨን
እርሱ ግን ይህ ሁሉ በላዩ ላይ ሲደርስ



www.ethiopianorthodox.org

የተናገረውን ቃል ኪዳኑን ሳይጥስ ፤
ሰዎች አፌዙበት ፍርድን ተቀበለ
ከወንበዴዎች ጋር አብሮ ተሰቀለ ።

ክርስቶስ ያንተ ሞት ለኛ ሕይወት ባይሆን
የሥቃይህ ነገር እንደምን በቆጨን

ከፈጠርከው ፍጥረት ታላቁ ሰው ሲሆን
ቢሠራም በስህተት የማይገባውን ፤

ኃጢአቱን ሳትቈጥር ሳትገነዘበው
ከንቱ ሆኖ እንዳይቀር አንተ ይቅር በለው ።

ክርስቶስ ያንተ ሞት ለኛ ሕይወት ባይሆን
የሥቃይህ ነገር እንደምን በቆጨን

## ክፍል ፪ ፤

ዋ የሰው ልጅ ሞኙ አሳዛኙ ፍጡር
ኃይል ካላነሰው ሲቻለው የማይምር ፨

ሰማይን በኮከብ ያዥጎረጎረውን
ምድርን በአበባ ያሽሞነሞናትን
በደመና ቀድቶ ሲያጠጣ መሬትን ፤

ውኃ ጠማኝ ቢለው ዋጋውን ሲከፍለው
ሐሞትና ከርቤ መጣጣም አጠጣው ።



ዋ የሰው ልጅ ሞኙ አሳዛኙ ፍጡር
ኃይል ካላነሰው ሲቻለው የማይምር

ነገሩን በውነት እንመራመረው
ኧረ ለመሆኑ እሱን የሰቀለው ከማን ላይ ቆሞ ነው ?

ዋ የሰው ልጅ ሞኙ አሳዛኙ ፍጡር
ኃይል ካላነሰው ሲቻለው የማይምር

አምላክ ፍቀድልን እኛ እናነጋግርህ
ሰው የበደል ሸክም ራሱ አሸክሞህ
እንደ ክፉ አድራጊ መልሶ ሲገርፍህ
የሰው ልጅ ከንቱነት እንደምን ይገርምህ

ዋ የሰው ልጅ ሞኙ አሳዛኙ ፍጡር
ኃይል ካላነሰው ሲቻለው የማይምር

በጎ ነገር እንጂ ክፉ አልተናገረ
አንደበትህ በጥም እንደምን ታሠረ

ዋ የሰው ልጅ ሞኙ አሳዛኙ ፍጡር
ኃይል ካላነሰው ሲቻለው የማይምር

እጆችህ በችንካር የተቸነከሩ
መሆኑ ነው እኮ ሰው ስለፈጠሩ
አንተ የፈጠርከው ሰው በዚችው ዕለት
ውለታን መልሷል ተቀበልለት

ዋ የሰው ልጅ ሞኙ አሳዛኙ ፍጡር
ኃይል ካላነሰው ሲቻለው የማይምር



www.ethiopianorthodox.org

## የትንሣኤ መዝሙር ፤

### ክፍል ፩ ፤

ቅዱስ ቅዱስ አልፋ /፫ ጊዜ
ይህንን ስቃይ ተቀበልክ ለኛ ተስፋ
ሳትቸገር ችግረኛ ሳትበድል በደለኛ

### ክፍል ፪ ፤

አምላኪየ መድኃኒቴ ነህ (፪ ጊዜ )
እንዴት ከፊትህ ትለየኛለህ
ንጹሑን ቅዱሱን ጌታ
ማን ይነግረኛል ያለበትን ቦታ ።

### ክፍል ፫ ፤

ከመቃብር ተነሥቷል ( ፫ ጊዜ)
ጠላቶችን ረግጦ በጭራሽ ደምስሷል
አሸንፎ ተነሣ የጨለማን ግዛት ለዘለዓለም
ለዘለዓለም ለመኖር በሰማዩ ገነት
ተነሥቷል ተነሥቷል ሃሌ ሃሌ ሉያ
ክርስቶስ ተነሥቷል



### ክፍል ፬ ፤

ይትፌሣሕ ሰማይ ወትትኃሠይ ምድር
ወይንፍሑ ቀርነ መሠረታተ ሕምዝ
ወይወውዑ አድባር ወአውግር
ወኵሉ ዕፀወ ገዳም ወዮምስ ዓባይ ፍሥሐ
በሰማያት ወምድርኒ ትገብር ፋሲካ
ተሐፂባ በደመ ክርስቶስ

(መዝሙረ ያሬድ)

### ክፍል ፭ ፤

አምላክ ተነሣልን ተነሣልን (፪ ጊዜ)
እልል እንበል ደስ ይበለን
ሞትን በሞት ደመሰሰልን
የሕይወት በርም ተከፈተልን
አምላክ ተነሣልን ተነሣልን (፪ ጊዜ)
የሲኦልን በሮች ሰባብሮ
አዳራሿንም ገብቶ በርብሮ
አምላክ ተነሣልን ተነሣልን (፪ ጊዜ )
እልል እንበል ደስ ይበለን



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፮ ፤

ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ

እምድኅረ ተንሥአ እሙታን
አስተርአዮን ቀዲሙ ለአንስት
ለማርያም ወላዲተ አምላክ
ወለማርያም መግደላዊት
ለሣራ ወለሰሎሜ ወለኵሎን ቅዱሳት አንስት

( መዝሙረ ያሬድ )

## ክፍል ፯ ፤

የአምላክ መነሣቱ ምንኛ ደስ ይላል (፪ ጊዜ)
መከራ ያየው (፫ ጊዜ) ለኛ መሆኑን ለተረዳ
የአምላክ መነሣቱ ምንኛ ደስ ይላል
ሕይወቱ ክርስቶስ መሆኑን
ላወቀ ለተረዳ ምእመን
የልብ ደስታን ይሰጣል
በሞቱ ሞተ ነፍስ መጥፋቱን
ከልብ ለሚያምን ክርስቲያን
የመንፈስ ነፃነት ይሰጣል ።



## ክፍል ፰ ፤

አምላክ ያለ በደል ሞተ ተቀበረ
ትእዛዙን አቃሎ አዳም ባስቸገረ ፤
ይኸው ሥጋ ሆኖ ተወልዶ ተገኝቶ
ከሲኦል አወጣው ደሙን ለሰው ሰጥቶ ፤
የተሰጠው ድኅነት በአምላክ መቀበር
ለኛ መድኃኒት ነው እንዳንቸገር
ትንሣኤክ እያለ ሁሉም ይዘምር ፤

ከነቅዓ ጥበብ ወንድም

## ክፍል ፱ ፤

ትንሣኤክ ለእለ አመነ ( ፪ ጊዜ )
ብርሃነከ ፈኑ ፤ ዲቤነ ። ( ፪ ጊዜ )

## ክፍል ፲ ፤

አማን በአማን ( ፪ ጊዜ )
ተንሣአ እምነ ሙታን ( ፪ ጊዜ )

( መዝሙረ ያሬድ )



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፲፩ ፤

ተገርፎ ተሰቅሎ የሞተው አንበሳ
ተገንዞ በጨርቅ ተቀብሮ እንደሬሣ
በሞት እጅ ተይዞ አልቀረም ተነሣ

እናምናለን ትንሣኤህን
በሥልጣንህ መነሣትህን
አርአያ ነውና ለሁላችን ፤

አፈር ቢረበረብ ሣጥን ቢደረደር
ድንጊያ በድንጊያ ላይ ደግሞም ቢነባበር
ምድር አልቻለችም አምላክን ለመቅበር ፤

እናምናለን ትንሣኤህን
በሥልጣንህ መነሣትህን
አርአያ ነህና ለሁላችን

አምላክ ስትነሣ ፈርሶ መቃብሩ
ሴቶች ትንሣኤህን ደፍረው ተናገሩ
እንሞታለን ብለው ማንንም ሳይፈሩ ።

እናምናለን ትንሣኤህን
በሥልጣንህ መነሣትህን
አርአያ ነውና ለሁላችን



እንግዲህ አልፈራም ሞትና ኩነኔ
አምላክ ከሞተልኝ ተሰቅሎ ስለኔ
ተደምስሷልና የሞት ሥልጣኔ

እናምናለን ትንሣኤህን
በሥልጣንህ መነሣትህን
አርአያ ነውና ለሁላችን ።

ከተሾመ ዘርይሁን

## ክፍል ፲፪ ፤

ክርስቶስ ተንሥአ እሙታን ( ፪ ጊዜ )
በዓቢይ ኃይል ወሥልጣን ( ፪ ጊዜ )

( መዝሙረ ያሬድ )

## ክፍል ፲፫ ፤

ክርስቶስ በሥልጣኑ ስለበረበራት
ሲኦል ተናገረች እንደዚህ በማለት
ወይኔ ሲኦል ሆይ በሥልጣኔ ስኖር
እንዴት እኮ ዛሬ እንደዚህ ልሸበር ፤

ክርስቶስ በሥልጣኑ ስለበረበራት
ሲኦል ተናገረች እንደዚህ በማለት



www.ethiopianorthodox.org

እኔ ቁሜ እየሔድኩ እያለ ሕይወቴ
ዘበኞቼ ሞቱ ተደፈረ ቤቴ

ክርስቶስ በሥልጣኑ ስለበረበራት
ሲኦል ተናገረች እንደዚህ በማለት

እስከ ዛሬ ድረስ ሥጋ የለበሰ አላሸነፈኝም
የዛሬው ሥጋ ግን ኃያል ሆኗል በጣም

ክርስቶስ በሥልጣኑ ስለበረበራት
ሲኦል ተናገረች እንደዚህ በማለት

ኃይሌ ተቀነሰ ጉልበቴም ደከመ
የሥልጣኔም ነገር በቃ ተፈጸመ

ክርስቶስ በሥልጣኑ ስለበረበራት
ሲኦል ተናገረች እንደዚህ በማለት

ነፍሳት እልል አሉ በዛ ደስታቸው
ፈጥኖ በመድረሱ ክርስቶስ ኃይላቸው ።

ክርስቶስ በሥልጣኑ ስለበረበራት
ሲኦል ተናገረች እንደዚህ በማለት ።

ከአእምሮ ማንደፍሮ



## የጳራቅሊጦስ መዝሙር ፤

### ክፍል ፩ ፤

ወጣቶች ሁላችን
ለክርስቶስ ታዛገሮች እንሁን በልጅነታችን

ክርስቶስ የኛ መሪ ሲሆን እኛ በልጅነት እንከተለው
ወጣቶች ሁላችን . .
ክርስቶስ ብርሃናችን ክርስቶስ ምግባችን ነው
ወጣቶች ሁላችን
ለክርስቶሰ ታዛገሮች እንሁን በልጅነታችን
ድል አድራጊው ክርስቶስ ነው
እርሱም ለኛ ምሳሌያችን ነው

ወጣቶች ሁላችን
ለክርስቶስ ታዛገሮች እንሁን በልጅነታችን

### ክፍል ፪ ፤

ጳራቅሊጦስ መንፈስ ቅዱስ ወረደ በተመረጡት ላይ
ወጣቶች ወጣቶች ወጣቶች እንመረጥ
እግዚአብሔር ወጣቶችን ይመርጣልና



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፫ ፤

አምላክ በነቢዩ በኢዩኤል አድሮ
ለኋለኛው ትውልድ ተናግሯል ዘርዝሮ
እግዚአብሔር ይላል በመጨረሻ ቀን
እንዲህ ይሆናል
ሥጋ በለበሰ ሁሉ [ላይ]
ከመንፈሴ አፈሳለሁ
ወንዶችና ሴቶች ልጆቻችሁ ትንቢት ይናገራሉ
ጐበዞቻችሁም ራዕይ ያያሉ
አምላክ በነቢዩ በኢዩኤል አድሮ
ለኋለኛው ትውልድ ተናግሯል ዘርዝሮ ።

ከአእምሮ ማንደፍሮ

## የሰንበት መዝሙር ፤

## ክፍል ፩ ፤

ጌታ በሰንበት ቀን ምን ትእዛዝ አዞናል
የወደቀን አንሱ ብሎ አስተምሮናል
የወደቀው ማነው ?
የወደቀውማ ኃጢአተኛው ሰው ነው



እንደምን እናንሣው
ከክርስቶስ ቃል ጋር በማስተዋወቅ ነው ፤
ደግሞስ ሌላ ተግባር ምን ማድረግ ያሻናል
ድኆችን መጐብኘት በጣም ያስፈልጋል ፤
አሁንስ ምን ቀረ ካዘዘው ፀባዖት
በሽተኞችና እሥረኞችን መጐብኘት
እርሱ በዚህ ዕለት ምን ትእዛዝ ፈጽሟል
በሽተኛን ሁሉ በመፈወስ ውሏል
ይኸን ለመፈጸም እንደምን ይቻላል ?
በተቻለ መጠን መሞከር ያሻናል ።

ከአእምሮ ማንደፍሮ

## ክፍል ፪ ፤

ሰንበተ ክርስቲያን የአማንያን ዕረፍት
ክብረ ምእመናን ብሥራተ ነቢያት
ፈጽሞ ከመራቅ ከሥጋዊ ፍትወት
መንፈሳዊ ሥራን የመንሠራባት ናት ።
አምላክ በጥበቡ ዓለምን ሲፈጥር
በስድስቱ ዕለታት ሁሉን ሲያቀናብር
ሕጉን ሲያስተላልፍ ሰዎችን ሲያስተምር
ምንም ሥራ አልሠራም ዕለቷን በማክበር ።



www.ethiopianorthodox.org

ሰንበተ ክርስቲያን የአማንያን ዕረፍት
ክብረ ምእመናን ብሥራተ ነቢያት
ፈጽሞ በመራቅ ከሥጋዊ ፍትወት
መንፈሳዊ ሥራን የምንሠራባት ናት ።

የአሪት አባቶች አፍላገ ሕገጋት
እየተመከሩ በነቢያት ትምህርት ፤
ደግሞም በመፈጸም የመጻሕፍትን ቃል
የሚገባ ክብርን ሲሰጧት ኑረዋል ፤

ሰንበተ ክርስቲያን የአማንያን ዕረፍት
ክብረ ምእመናን ብሥራተ ነቢያት
ፈጽሞ ከመራቅ ከሥጋዊ ፍትወት
መንፈሳዊ ሥራን የምንሠራባት ናት

በሰው ፊት ተገልጾ በኋላም እግዚአብሔር
አንድ ልጁን ልኮት ዓለምን ሲያስተምር ፤
ሙታን አስነሥቷል ድውዩን ፈውሷል
የሰንበትንም ክብር በዚህ ዓይነት ገልጿል ።

ሰንበተ ክርስቲያን የአማንያን ዕረፍት
ክብረ ምእመናን ብሥራተ ነቢያት
ፈጽሞ በመራቅ ከሥጋዊ ፍትወት
መንፈሳዊ ሥራን የምንሠራባት ናት



በመንፈስ ተቃኝተን ከልብ ብናየው
እርሱን ለመከተል ምሳሌው ግልጽ ነው ፤
በሕግ ተገደን ምንም ሥራ ባንተው
ጥቅምን የሚሰጥ ግን ከልብ ማክበር ነው ።

ሰንበተ ክርስቲያን የአማንያን ዕረፍት
ክብረ ምዕመናን ብሥራተ ነቢያት
ፈጽሞ በመራቅ ከሥጋዊ ፍትወት
መንፈሳዊ ሥራን የምንሠራባት ናት

ድኅነ ካልጐበኘን በዚህች በሰንበት ቀን
ምንም ትርጉም የለው ላንድ ክርስቲያን
ስለዚህ ትምህርቱን ከልብ ተከታትለን
በዚች ቀን ደግ ሥራን መፈጸም አለብን ።

ሰንበተ ክርስቲያን የአማንያን ዕረፍት
ክብረ ምእመናን ብሥራተ ነቢያት
ፈጽሞ በመራቅ ከሥጋዊ ፍትወት
መንፈሳዊ ሥራን የምንሠራባት ናት ።

## የጸሎት መዝሙር ፤

አቤቱ በስምህ አድነን
ልመናችንንም ተቀበለን
አቤቱ በስምህ አድነን
መድኃኒታችን አንተ ነህና



www.ethiopianorthodox.org

አቤቱ በስምህ አድነን
ባንተም አዳኝነት እንመካለን
አቤቱ በስምህ አድነን
የቀናውን መንገድ እንድትመራን
መልካም ፈቃድህ ይሁንልን ።
አቤቱ በስምህ አድነን

## የክረምት መዝሙር ፤

### ክፍል ፩ ፤

እንደርሱ በጽርሐ አርያም የሚኖር ማነው
መሠረቱን የሚሠራ ማነው
የምድርን መሠረት ተሸክሞ በጠፈር የሚኖር ማነው ?
ምድርን ከውኃ ላይ ይፈጥራል(ወይም ያቆማል ያንሳፍፋል)
በረቂቅም ይጠቀልላል
በአሸዋም ይወስናል
በነፋስ ያጸናል
ውኃን ታቶ ሰማይ ይለዋል ።

ከአእምሮ ማንደፍሮ

### ክፍል ፪ ፤

እግዚአብሔር ኢዮብን በደመና ጠየቀው
እንዲህም አለው



ምድርን የመሠረትኳት ከምን ላይ ነው
ገመድስ ያዞርኩባት ምን ያህል ነው
ኢዮብም መልሶ አለው
አቤቱ አቤቱ ሁሉንም ታውቃለህ አንተው

ከነቅዓ ጥበብ ወንድም ፤

## መዝሙረ ንስሐ ፤

### ክፍል ፩ ፤

አቤቱ ምሕረትህን ከኔ አታርቅብኝ
ቸርነትህና ይቅርታህ ይገውብኙኝ
ኃጢአቶቼ ያዙኝ ማየትም ተሳነኝ
እንደራሴ ጠጉር በላዬ ከበቡኝ
እንዳልቀር ወድቄ በደሌ ጨልሞኝ
የድኅነቴ ፋና አምላኬ አንተ ሁነኝ

ከአእምሮ ማንደፍሮ ፤

### ክፍል ፪ ፤

አንተን በማመስገን ክብርህን ለመውረስ
የፈጠርኸን ሁሉ በሕይወት እስትንፋስ
የለህም እንዳንል አውቀናል መኖርህን
ጠፍተንስ ብንሔድ ወዴት እንደርሳለን



www.ethiopianorthodox.org

ከሰማይ ብንወጣ ያንተ ነው ግዛቱ
ከምድር ብንሸሸግ ያንተ ነው ግዛቱ
ከባሕር ብንገባ ያንተ ነው መንግሥቱ ፤
ሁለት ክንፍ አውጥተን ብንበር እንዳሞራ
አንተ የሌለህበት የት ይገኛል ሥፍራ ።
ሕያው የሕያው ልጅ አልፋና ኦሜጋ
ንስሐን ስጠነ ወዳንተ የሚያስጠጋ ።

ከአእምሮ ማንደፍሮ ፤

## ክፍል ፫ ፤

ለሰው ልጅ ተገለጠ አስደናቂ ሥራ
በሁለት ዓሣ በአምስት የገብስ እንጀራ
ስላጠገባቸው ኢየሱስ ሊቀ ሐራ
ለአምስትሺህ ሰዎች ለነበሩት ከእርሱ ጋራ
ሣር በመላበት በለመለመ ሥፍራ ፤
አንድ ልጅ ነበረ ካባቱ የራቀ
ገንዘቡን አባክኖ ጥሪቱን ያወቀ
ወደ አባቱ ሔዶ እግሩ ላይ ወደቀ
እጅግም ተፀፅቶ ንስሐ ስለጠየቀ
ይቅርታም አገኘ ካባቱ ታረቀ ፤
እኛም ብንበድል ግብራችን ቢከፋ
በጸሎት እንቅረብ ከርሱ ዘንድ አንጥፋ
የአምላክ ቸርነት በኛ እንዲንሰራፋ



ተግባራችን ተቃንቶ አምሮ ከተስፋፋ
ይፈጸምልናል የተሰጠን ተስፋ

ከነቢየ ልዑል ዮሐንስ

## የእመቤታችን መዝሙር ፤

## ክፍል ፩ ፤

ሰላም ላንቺ ይሁን እመቤቴ ማርያም ( ፪ ጊዜ )
በመላኩ በገብርኤል ሰላምታ ሰላም እልሻለሁ
በአሳብሽ ድንግል ነሽ
በሥጋሽም ድንግል ነሽ
ከሴቶች ሁሉ አንቺ የተባረክሽ ነሽ
የማኅፀንሽም ፍሬ የተባረከ ነው
ያሸናፊው የአምላክ እናት ሆይ
ከልጅሽ ይቅርታን ለምኝልን ።

## ክፍል ፪ ፤

ሰላም ሰላም ሰላም ሰላም ( ፬ ጊዜ ) ማርያም ድንግል
ልመናሽ ለሚያምኑ ድኅነት ያሰጣል
ስላም ሰላም ሰላም ሰላም ማርያም ድንግል
ደቀ መዛሙርቱ በአሳብ ሲዋኙ
ይኸው በቅርብ ጊዜ ምልክት አገኙ



www.ethiopianorthodox.org

ሰላም ሰላም ሰላም ማርያም ድንግል
ልመናሽ ለሚያምኑ ድኅነት ያሰጣል
ለኛ ለልጆችሽ ኃጢአት ላደከመን
ከልጅሽ ይቅርታን ድንግል ለምኝልን
በሐና በኢያቄም እመቤታችን
በዚች ቀን ባርኪልን ማኅበራችንን ።

ሰላም ሰላም ሰላም ማርያም ድንግል
ልመናሽ ለሚያምኑ ድኅነት ያሰጣል

## ክፍል ፫ ፤

የመቃብር ቦታ አንቺ ጌቴ ሴማን
እሳተ መለኮት የተሸከመውን
ከቶ እንደምን ቻልሽው አካለ ድንግልን
በጣም ያስገርማል ያንችውም ሁኔታ
እንደ ቅድስቲቱ እንደ ጎልጎታ

የመቃብር ቦታ አንቺ ጌቴ ሴማን
እሳተ መለኮት የተሸከመውን
ከቶ እንደምን ቻልሽው አካለ ድንግልን ።

የመቤታችን ክብር የተረዱ ሁሉ
ዝናሽን ለመንገር በጣም ይጓጓሉ



የመቃብር ቦታ አንቺ ጌቴ ሴማን
እሳተ መለኮት የተሸከመውን
ከቶ እንደምን ቻልሽው አካለ ድንግልን ።

## ክፍል ፬ ፤

የብርሃን መውጫ የሕይወት መሰላል
የተነበየላት ነቢዩ ሕዝቅኤል
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
ሁና የተገኘች ያምላክ ማኅደር
የዳዊት መሰንቆ የጌዴዎን ፀምር
በገነት መካከል ያለች ለምለም ሣር
አፍርታልናለች ያለወንድ ዘር ፤
እስቲ እናመስግናት እንዲህ በማለት
ቅድስት እናታችን ስብሕት ወቡርክት
አንቀጸ ብርሃን መዓርገ ሕይወት
አዘክሪን ድንግል ለልጅሽ በውነት
በደህና እንዲያደርሰን ለመጪው ዓመት
እንድናገኝ ፍቅርን እንደሐዋርያት
እንደመቤታችን አርምሞ ትዕግሥት
ያድለን ፈጣሪ ፍጹም መድኃኒት ።

ከማኅበረ ክርስቶስ



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፫ ፤

በሔዋን አጥፊነት የነበር ተዘግቶ
የአዳም ልጅ ሁሉ እሳት ባሕር ገብቶ
ዳግም እንዲከፈት በሥጋዊ ምሥጢር
ፈቃዱ የሆነ ይመስገን እግዚአብሔር ፤
በረቂቅ ሥልጣንህ ከድንግል ተወልደህ
እኛንም ያዳንከን ሞትን ድል አድርገህ
ማኅበራችንን ባርክልን እባክህ ፤
ደኅና ያቆየሽን ከጧት እስከ ማታ
ምስጉን ሆይ ተመስገን ልዑል የኛ ጌታ ።

ከወ/ ት/ ዓፀደ ክርስቶስ ተፈራ

## ክፍል ፬ ፤

ሰላም ላንቺ ይሁን እንሰግድልሻለን
እናታችን ማርያም እንማልድሻለን
ነፍሴ እግዚአብሔርን ታላቅ ታደርጋለች
መንፈሴም በአምላኬ ደስ ትሰኛለች ፤
ዐይቷልና የባሪያዩቱን መዋረድ
ያመሰግኑኛል ከእንግዲህ ትውልድ
ከአሸናፊያችን ከይሲ ጠላታችን
ተማልደናል ባንቺ እንድታድኝን ፤



ብርቶችን አዋርዶ ከዙፋናቸው
የተዋረዱትን ከፍ አረጋቸው ።
በጎ ነገር መላ የተራቡትን
ባዶ እጅ ሰደደ ባለጠጎችን
በሐና በኢያቄም እመቤታችን
በዚች ቀን ባርኪልን ማኅበራችንን
ተቀበል እንግዲህ እሥራኤል ባሪያህን
ይቅርታንም አስብ ለአባቶች ያልከውን
ለአባቶች አባት ለአብርሃም ለዘሩም
እንዲሆን ምህረቱ እስከ ዘለዓለም ፤
በሐና በኢያቄም እመቤታችን
በዚህ ቀን ባርኪልን ማኅበራችንን

ወ/ ት ዓፀደ ክርስቶስ ተፈራ

## ክፍል ፭ ፤

ተናገረ እዝራ ተናገረ
ዳዊት ዘመረ
ተናገረ እዝራ ተናገረ
ዳዊት ዘመረ
ዕዝራ ባመሰንቆ እያጫወታት
ሳታውቀው አለፈች ያን መላከ ሞት



www.ethiopianorthodox.org

ውኖች ቀለም ሁነው፤እንጨቶችም ብዕር
ቢጽፉት አያልቅም የማርያምን ክብር፤።

## የደብረ ታቦር መዝሙር ፤

ሰላም ሰላም ሰላም ሰላም የታቦር ተራራ
ብርሃነ መለኮት ባንተ ላይ፤አበራ
ሰላም ሰላም ሰላም ሰላም የታቦር ተራራ
ሙሴና ኤልያስ እንዲያ ሲሸበሩ
ምነው አንተ አልፈራህ እንዴት ነው ምሥጢሩ ።

ሰላም ሰላም ስላም ሰላም የታቦር ተራራ
ደቀ መዛሙርቱ ከርሱ፤ጋር የዋሉ
ያምላክን ድምፅ ሰምተው ለመፅናት አልቻሉ
ሰላም ሰላም ሰላም ሳላም የታቦር ተራራ
ብርሃነ መለኮት ባንተ ላይ አበራ

## የቤተ ክርስቲያን መዝሙር ፤

### ክፍል ፩ ፤

እንኳን ደኅና መጣችሁ ፣ እንኳን ደህና መጣችሁ
ወደኔ ወደ እናታችሁ ፤ እጄን ዘርግቼ ስጠብቃችሁ
ወላጆቻችሁን እንድታከብሩ ፤ አምላካችን መናገሩ



እንድትፈጽሙ ትእዛዙን ፤ እንቢተኞች ባለመሆን
በከንቱ አይደለም የሰጠን ሕጉን
እንኳን ደህና መጣችሁ ፤ እንኳን ደህና መጣችሁ
የዕውቀት ገበያተኞች እንደመሆናችሁ
ምንም ጊዜ ባይኖራችሁ
እንኳን ደህና መጣችሁ ፣ እንኳን ደህና መጣችሁ
እንደዚህ እኮ የምላችሁ
ቤተ ክርስቲያን ነኝ እናታችሁ
ስለመጣችሁ እናንት ልጆቼ
ታዩኝ አላችሁ ተደስቼ ተደስቼ
ከሰኞ እስከ ዓርብ እየሠራን
እንጠያየቅ በሰንበት ቀን፤በሰንበት ቀን
እንኳን ደኅና
ከአእምሮ ማንደፍሮ

### ክፍል ፪ ፤

ሰላም ለኪ፤እናታችን ቤተ፤ክርስቲያን ( ፪ ጊዜ )
በደሙ የዋጀሽ በደሙ የዋጀሽ ( ፬ ጊዜ፤)
ኢየሱስ መድኅን፤( ፪ ጊዜ )



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፫ ፤

የዘለዓለም ቤቴ ፤ የዘለዓለም ቤቴ
እግዚአብሔር ነው መድኃኒቴ የዘለዓለም ቤቴ
እስካሁን ሳላውቀው በከንቱ ፤ ስደክም
ወደርሱ በመቅረብ ዳንኩኝ ለዘለዓለም

    የዘለዓለም ቤቴ የዘለዓለም ቤቴ
    እግዚአብሔር ነው መድኃኒቴ የዘለዓለም ቤቴ

በከንቱ የምትደክሙ አሁንም ካላችሁ
ወደርሱ ተጠጉ እኔ ልምከራችሁ

    የዘለዓለም ቤቴ የዘለዓለም ቤቴ
    እግዚአብሔር ነው መድኃኒቴ ፤ የዘለዓለም ቤቴ

## የዘወትር መዝሙር ፤

## ክፍል ፩ ፤

በጭራሽ እንዲደርቅ የኃጢአት ሥሩ
መበርታት አለበት ሁሉም በተግባሩ ፤

    በሃይማኖት በሃይማኖት ፤ አለብን መፅናት ( ፪ ጊዜ )

እንፅና በመንፈስ አንሁን ልበመንታ
እንዲከፈትልን ደጁን ስንመታ ።



    በሃይማኖት በሃይማኖት ፤ አለብን መፅናት ( ፪ ጊዜ )

ሕይወትን የሚሰጥ ወደአብ የሚወስድ
ከኢየሱስ በቀር የለም ሌላ መንገድ

    በሃይማኖት በሃይማኖት ፤ አለብን መፅናት ( ፪ ጊዜ )

ምግባራችን አምሮ በእምነት ከፀናን
ሲያበራ ይኖራል የሥራችን ብርሃን

    በሃይማኖት በሃይማኖት ፤ አለብን መፅናት ( ፪ ጊዜ )

ይብዛ ስላማችን መልካም ሥራ እንሥራ
የመንፈስን ፍሬ ሁላችን እናፍራ

    በሃይማኖት በሃይማኖት ፤ አለብን መፅናት ( ፪ ጊዜ )

ከነቢየ ልዑል ዮሐንስ

## ክፍል ፪ ፤

ለአማልክት አምላክ ለጌታዎች ጌታ
ለኛም ለሆነልን ጋሻና መከታ
ክብሩን በመናገር እንዘምር በልልታ ፤
ክብሩን ጌትነቱን ለማያውቁ ሁሉ
እንዲያውቁ ለማድረግ በዚህ ዓለም ሳሉ
መናገር አለብን ሁላችን በሙሉ ፤
የቀና አንደበትን ያላገኙት እንኳን



www.ethiopianorthodox.org

አራዊት እንስሳት ዕፀዋት አዕባን
ሲያቀርቡ ይታያል ለአምላክ ምስጋናን ፤
ፍጥረታት ሁላቸው ለሚያመሰግኑት
ከርሱ በተገኘው በቀናው አንደበት
እስኪ ሁላችንም እንዘምርለት ።

ከአእምሮ ማንደፍሮ

## ክፍል ፫ ፤

የእግዚአብሔር ስም ይቀደስ
በሁላችንም ዘንድ ይወደስ
እንዲያድርብን የርሱ መንፈስ
እንታደስ እንታደስ
ክብሩ በእኛ ይንገሥ ፤
ለኢየሱስ እናቅርብ ጸሎት
ሁላችንም እንስገድለት
ሁኗልና ስለእኛ መሥዋዕት ፤
እንታደስ እንታደስ
ክብሩ በኛ ይንገሥ
ምእመናን ሁሉ ወደፊት እንግፋ
ሥራችንም እንዲስፋፋ
ተሰጥቶናልና ብዙ ተስፋ



እንታደስ እንታደስ
ክብሩ በእኛ ይንገሥ
ከሠሪ ጋር ካልተሠለፈ
ፈተናውንም ካለለፈ
ሥፍራም የለው ለሰነፈ ፤
እንታደስ እንታደስ
ክብሩ በኛ ይንገሥ
ተግባራችን ይተባበር
በዚህ ዓለም ላይ ስንኖር
ይህ ካልሆነ የለም መከበር ፤
እንታደስ እንታደስ
ክብሩ በኛ ላይ ይንገሥ
ሁላችንም እንሁን ጠንካራ
በስንፍና አንመራ
ስለሚጠብቀን ብዙ ሥራ
እንታደስ እንታደስ
ክብሩ በኛ ይንገሥ ።

ከነቢየ ልዑል ዮሐንስ

## ክፍል ፬ ፤

ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ



www.ethiopianorthodox.org

ለአብና ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስም
ምስጋና ከማቅረብ ከቶ አንወሰንም
ዛሬም ወደፊትም ደግሞም ለዘለዓለም
ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ

ከዚህ ከማራኪው ካሸናፊው ዓለም
የጠራ ይድናል የፈጣሪውን ስም
በውነት ያለ ሐሰት ያለ ጥርጥርም
ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ

ከቶ መድኃኒቱን የሚጠላ የለም
ኑሯችን እንዲያምር አንድነታችንም
ሊኖረን ይገባል ፍቅርና ሰላም ፤
ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ

ያልኸውን አስበህ እናንተ ሁላችሁ
ሁለት ሦስት ሁናችሁ በስሜ ካላችሁ
እኔም እገኛለሁ በመካከላችሁ
ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ



አቤቱ አምላክ ሆይ እንለምንኻለን
እንድትገኝልን በመካከላችን
ይኸው ተገኝተናል ሁለት ሦስት ሁነን
ስብሐት ለአብ ስብሐት ለወልድ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ

ከተሾመ ዘርይሁን

## ክፍል ፫ ፤

በሸክማችሁ ክብደት የተጨነቃችሁ
የከበደውን ሸክም እንዳቀልላችሁ
ሁላችሁ ወደኔ መምጣት አለባችሁ ፤
እንድትሸከሙ ቀላሉን ቀንበሬን
ጽድቅን ከኔ መማር ፈቃዳችሁ ይሁን ።

በሸክማችሁ ክብደት የተጨነቃችሁ
የከበደውን ሸክም እንዳቀልላችሁ
ሁላችሁ ወደኔ መምጣት አለባችሁ

ፈቃደኛ ሆኖ የሚሸከም ካለ
ቀንበሬም ልዝብ ነው ሸክሜም የቀለለ

በሸክማችሁ ክብደት የተጨነቃችሁ
የከበደውን ሸክም እንዳቀልላችሁ
ሁላችሁ ወደኔ መምጣት አለባችሁ



www.ethiopianorthodox.org

ይቅርታን የማደርግ አምላክ ስለሆንኩኝ
ለነፍሳችሁ ዕረፍት እሰጣታለሁኝ ፤
በሸክማችሁ ክብደት የተጨነቃችሁ
የከበደውን ሸክም እንዳቀልላችሁ
ሁላችሁ ወደኔ መምጣት አለባችሁ

ከአእምሮ ማንደፍሮ

## ክፍል ፮ ፤

የአብ ሰላም የወልድ ፍቅርም የመንፈስ ቅዱስ አን
ድነትም
ይደር ፤ በመካከላችሁ የሰላም አምላክ ይኑር ከሁላችሁ ከሁ
ላችንም ጋር ፤

## ክፍል ፯ ፤

ጴጥሮስ ወጳውሎስ የዓለም ብርሃናት
ወንጌልን ሰበኩ ለዓለም ድኅነት
የሰው ልጅ እንዳይተው የነሱን ትምህርት ፤
ሐዋርያት ዘርተው ሲለቀም በሻማ
ሰዎች አትለዩ ከወንጌል አውድማ
ዘለዓለም ማጥገቡ ተሰምቷል በራማ ፤
የዘለዓለም ሕይወት ማግኘት ያማራችሁ



የሐዋርያት ሥራ ይሁን ዓላማችሁ
ሰማያዊው አባት ቦታ እንዲሰጣችሁ ።

ከነቅዓ ጥበብ ወንድም

## ክፍል ፰ ፤

ሕዝብህን አድነን ርስትህን ባርከህ
የማቸነፍን ኃይል ለባሮችህ ሰጥተህ
ስምህን ስንጠራ ጠብቀን እባክህ ።
አቤቱ በሌሊት ስምህን ስናስብ
ሕግህን ተረድተን ጠብቀን ከልብ
ትእዛዝህን ፈጸምን በፍርሃት ጥበብ ፤
አቤቱ ጌታችን ከኛ እንዳትርቀን
ስምህን ስናነሳ እንድትሰማን
አንተ ካልሰማኸን ሌላ አምላክ የለነ ፤
እንደቸርነትህ ሁላችን ከጸደቅን
በእግዚአብሔር ይሁን እምነታችን
ወደአምላክም ጸጋ በእምነት መግባትን

ከነቅዓ ጥበብ ወንድም

## ክፍል ፱ ፤

መልካም እንድንሠራ ባንድ ላይ ሆነን
አቤቱ ባርክልን ማኅበራችንን



www.ethiopianorthodox.org

ሁላችንም ብናምን ካንድ ሁለት መሻሉን
ምን ጊዜም እርዳታ ካንተ እንሻለን

መልካም እንድንሠራ ባንድ ላይ ሆነን
አቤቱ ባርክልን ማኅበራችንን

ሁለት ወይም ሦስት ሆነን ብንኖር
አንተም ትገኛለህ ፍጹም ከኛ ጋር

መልካም እንድንሠራ ባንድ ላይ ሆነን
አቤቱ ባርክልን ማኅበራችንን

ጌታ ይኸነን ቃል አንተ ያወጅኸውን
ያንተ ተከታዮች በደንብ እናምናለን

መልካም እንድንሠራ ባንድ ላይ ሆነን
አቤቱ ባርክልን ማንበራችንን

ከአእምሮ ማንደፍሮ

## ክፍል ፲ ፤

ጳውሎስ እንዲህ አለ ዓለም ከነክፉ ሥራው ያል
ፉልና ወንድሞቸ ተዘጋጁ መልካም ሥራ ለመሥራት እኔ
ግን ሩጫዬን ጨረስኩ ሃይማኖቴንም ጠብቅሁ
እንግዲህ ተዘጋጅቻለሁ፤ እውነተኛ ፈራጅ
ኢየሱስ የሚሰጠኝን አክሊል ለመቀበል



## ክፍል ፲፩ ፤

ተነሡ እንዘምር ተነሡ እንዘምር ተነሡ
እንዘምር ለአምላክ ባንድ ቃል
ሁላችንም እንጂ ወንድ ሴት አንበል
የአምላክ ምስጋና ምን ያሳፍረናል
እንኳንስ እሱና ሰው ይመሰገናል

ተነሡ እንዘምር ተነሡ እንዘምር ተነሡ
እንዘምር ለአምላክ ባንድ ቃል
ሁላችንም እንጂ ወንድ ሴት አንበል፤
ለሚያወርድልን ዝናመ ምሕረት
ደግሞም ለሚሰጠን እክለ በረከት

ተነሡ እንዘምር ተነሡ እንዘምር ተነሡ
እንዘምር ለአምላክ ባንድ ቃል
ሁላችንም እንጂ ወንድ ሴት አንበል
ሁሉንም በጊዜው ለሚሰጠን ጌታ
መዘመር አለብን ሁላችን በልልታ ፤

ተነሡ እንዘምር ተነሡ እንዘምር ተነሡ
እንዘምር ለአምላክ ባንድ ቃል
ሁላችንም እንጂ ወንድ ሴት አንበል

ከአእምሮ ማንደፍሮ



www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፲፪ ፤

አባታችን ሆይ የምትኖር በሰማይ
መንግሥትህ ትምጣልን ክብርህን እንድናይ
ፈቃድህ በሰማይ ሕይወት እንደሆነ
እንዲሁም በምድር ሰላምን ስጠነ ፤
ስጠን ሲዛሬ የዕለት ምግባችንን
በደላችንንም ይቅር እንድትለን ፤
ጌታ ሆይ አታግባን ከክፉ ፈተና
አንተ ካረዳኸን ኃይል የለንምና ፤
ኃይልና ምስጋና መንግሥትም ያንተው ናት
አሜን ለዘላለም ይሁንልን ዕረፍት ።

## ክፍል ፲፫ ፤

አቤቱ ከክፉ ሰው አድነን
በልባቸውም ክፉ ካሰቡ
ከአመፀኞች ሰዎች ጠብቀን
ካመፀኞች ሰዎች
አቤቱ ከኃጢአተኞች እጅ አውጣን
እርምጃችንም ሊያረክሱ ካሉ
ከሰነፎች ወጥመድ ሠውረን
ከሰነፎች ወጥመድ



ወዳንተ ስንጮህ ቃላችን አዳምጥ
ጸሎታችንንም በፊትህ ተቀበለን
እጅ መንሳታችን መሥዋዕት ትሁነን
አቤቱ ለአፋችን ጠባቂ አኑር
የከንፈሮቻችን መዝጊያ ጠብቅ
ልባችንንም ወደ ክፉ አትመልስ
ወደ ክፉ አትመልስ
በአንተ ያመነች ነፍስን አትጣላት
የዘለዓለም ዕረፍት ስጣት
ሁሉም ባንተ ዘንድ ይቻላልና
የዘለዓለም ዕረፍት ።

## ክፍል ፲፬ ፤

ሰዎች ሁላችንም ( ፪ ጊዜ )
መፋቀር አለብን በዚች ዓለም ( ፪ ጊዜ )
ከተፋቀርን በዚች ዓለም ( ፪ ጊዜ )
ክብር እናገኛለን ከአዲሱ ዓለም ( ፪ ጊዜ )
ሰዎች ሁላችንም . .
መፋቀር አለብን በዚች ዓለም . .
ከተፋቀርን በዚች ዓለም . .
ክብር እናገኛለን ከአዲሱ ዓለም
ጌታችንም ብሏል ፍቅርን ያዟት
አምላካችን ብሏል ፍቅርን ያዟት



www.ethiopianorthodox.org

የሕይወት በር ቁልፍ መክፈቻ እርሷ ናት (፪ ጊዜ)
ሰዎች ሁላችንም ˎ .

መፋቀር አለብን በዚች ዓለም . .
ከተፋቀርን በዚች ዓለም . .
ክብር እናገኛለን ከአዲሱ ዓለም . .

እግዚአብሔር ከሰጠን ከአሥሩ ቃላት
እግዚአብሔር ከሰጠን ከአሥሩ ቃላት
ወንድምኽን ውደደው የምትል አንዷዋ ናት
ወንድምኽን እንዳንተው አፍቅር የምትል ናት ፤

ሰዎች ሁላችንም . .
መፋቀር አለብን በዚች ዓለም . .
ከተፋቀርን በዚች ዓለም . .
ክብር እናገኛለን ከአዲሱ ዓለም . .

ሕይወት እንድናገኝ በፍቅር ተባብረን
ሕይወት እንድናገኝ በፍቅር ተሳስረን
ምሕረቱ የማያልቅ አምላካችን ይርዳን
ምሕረቱ የማያልቅ አምላካችን ይርዳን ፤

## ክፍል ፲፫ ፤

ወጣቶች ተው ተመለሱ ወጣቶች ተው ተመለሱ
ወጣቶች ተው ተመለሱ



መንገዱን የጥንቱን አትርሱ መንገዱን የጥንቱን አትርሱ
መንገዱን የጥንቱን አትርሱ

ወጣቶች ተው ተመለሱ (፫ ጊዜ)

መንገዱን ስታችሁ ስትገሠግሡ ገደል ልትገቡ ነው
ተው ተመለሱ ።

ወጣቶች ተው ተመለሱ (፫ ጊዜ)

ወጣቶች ስሙ እባካችሁ ፤ ኑ በዚህ እኛ እናሳያችሁ

ወጣቶች ተው ተመለሱ (፫ ጊዜ)

ቤተ ክርስቲያን ቅድስት እናታችሁ ፤ ተነሥታለች
ልትቀበላችሁ ።

ወጣቶች ተው ተመለሱ (፫ ጊዜ)

ወጣቶች ልጆቿ ሁላችሁ ፈልጓት እየጠየቃችሁ
ተነሥታለች ልትቀበላችሁ
ወጣቶች ተው ተመለሱ ወጣቶች ተው ተመለሱ
ወጣቶች ተው ተመለሱ መንገዱን የጥንቱን አትርሱ
መንገዱን የጥንቱን አትርሱ ።

ከበላይ ተገኘ ።

## የቅዱሳን መዝሙር ፤

አበው ጸልዩ በእንቲአነ
ጸሎትክሙ ትባርከነ



www.ethiopianorthodox.org

የቅዱሳን ጸሎት ያባቶች ልመና
ከኃጢአት በሽታ ይፈውሳልና ።

አበው ጸልዩ በእንቲአነ
ጸሎትክሙ ትባርከነ

የሕጉን መሠረት ስለ አደረጋችሁ
ለቤተ ክርስቲያን አዕማድ ሆናችሁ ።

አበው ጸልዩ በእንቲአነ
ጸሎትክሙ ትባርከነ

ወደኛ ስትመጡ እናንተ ጳጳሳት
የክርስቲያን ደሴት ኢትዮጵያ ደስ አላት

አበው ጸልዩ በእንቲአነ
ጸሎትክሙ ትባርከነ

ከአእምሮ ማንደፍሮ

## የአብርሃም መዝሙር ፤

አብርሃም ወሰዶ ለይስሐቅ ወልዱ (፪ ጊዜ)

ከመ ይሡዖ አውረደ ሎቱ
ቤዛሁ በግዐ እኁዝ አቅርንቲሁ
በዕፀ ሳቤቅ ዕፀ ሳቤቅ ብሂል
ዕፀ ሥርየት መስቀል ።

( መዝሙረ ያሬድ )



## የምጽአት መዝሙር ፤

አምላክ አመጣጥህ ባምን ይታወቃል
መረጃ የሚሆን ምን ምልክት ይዟል
ያለሙስ ፍጻሜ እንደምን ይሆናል ፤

ብለው ሲጠይቁ ደቀመዛሙርትህ
እንዳስረዳኻቸው ምሳሌን መስለህ ።

ኃጢአት እንዳንሠራ ያችን ቀን ዘንግተን
ፈቃድህ ሆኖልን ማስተዋልን ስጠን

ለማስታዋስማ እንኳንስ ቃልህን ደግሞም ምሳሌውን
ደብረ ዘይትን ሳይቀር እናስታውሳለን ።

ምሳሌውን ዓይተን መምጣትህን ብናምንም
ያላንተ አንድ ነገር ሊፈጸም አይችልም
ስለዚህ ጌታ ሆይ ይቅርታህ ከኛ ጋር ይሁን ለዘለ
ዓለም ።

ከአእምሮ ማንደፍሮ



www.ethiopianorthodox.org